# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# የመንግስት የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለስልጣን

## መመሪያ ቁጥር 172/2017

## የልማት ድርጅቶች ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ

**መጋቢት 2017 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# <u>የልማት ድርጅቶች የማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 172/2017</u>

የመንግስት ልማት ድርጅቶች የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማሳካት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ባላቸው ሚና ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊ እንዲሁም የሠራተኛውን ጤንነትና ደህንነት የመጠበቅ እና የማህበረሰቡን ማህበራዊ እድገት የመደገፍ ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ፤

የመንግስት ልማት ድርጅቶች ዓላማቸውን ለማሳካት ከሚያደርጉት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጐን ለጐን የማህበረሰቡ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የሥራቸው አንድ አካል አድርገው መያዛቸው ከማህበረሰቡ ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዲፈጥሩ የሚያስችላቸው በመሆኑ፤

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን መወጣት ያለባቸው በገበያ ውስጥ የሚኖራቸውን ተወዳዳሪነትና ትርፋማነት ጠብቀው መሆን ስለሚገባው እነዚህን ጎን ለጎን ማስኬድ የሚያስችል ግልጽ አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የመንግስት የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለስልጣን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ እንደገና ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 159/2016 አንቀጽ 11 እና አንቀጽ 57 መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 172/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
2) **"የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት"** ማለት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላሉበት የአካባቢ ህብረተሰብ ያለባቸውን ችግሮች ባላቸው አቅም በማቃለል ወይም በህግ የተቀመጡ

ማህበረሰብ ነክ ግዴታዎችን ለመወጣት ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ውጤት ያላቸውን ተግባራት በመፈፀም የሚሰጡት አገልግሎት ነው፤

3) **"የስራ አመራር"** ማለት ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና ተጠሪነታቸው ለዋና ሥራ አስፈፃሚ የሆኑ የልማት ድርጅቱ የሥራ አመራር አባላት ናቸው፤

4) በደንብ ቁጥር 159/16 ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት ወይም ሃረጋት ለዚህ መመሪያም ተመሳሳይ ፍቺ የሚኖራቸው ይሆናል።

5) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

6) በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ያካትታል።

**3. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ ለባለስልጣኑ ተጠሪ የሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## መመሪያው የሚመለከታቸው አካላት ተግባርና ኃላፊነት

**4. የባለስልጣኑ ተግባርና ሃላፊነት**

ለባለሥልጣኑ በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ትግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለው ሚና ይኖረዋል፡-

1) የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ በሁሉም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

2) በልማት ድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ የሚቀርበውን የልማት ድርጅቱን ስትራቴጂክና ዓመታዊ የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ ዕቅድ ያጸድቃል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

3) የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አፈጻጸም የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ በሚታዩ ክፍተቶች የማስተካከያ ዕርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

4) ከልማት ድርጅቶች ወቅታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶች እንዲቀርቡ ያደርጋል፣ አፈጻጸማቸውን በመገምገም ተገቢውን ግብረ-መልስ ይሰጣል፤ ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራል።

## 5. የቦርድ ተግባርና ሃላፊነት

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ እንደገና ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 159/2016 የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የሚከተለው ተግባርና ሃላፊነት ይኖረዋል፦

1) የልማት ድርጅቱ የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከተታተላል፤

2) የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት ተግባራዊ የሚሆንበት አቅጣጫ፣ አግባብ፣ ወሰንና ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮችን ይወስናል፤

3) የልማት ድርጅቱ የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት ስራዎች በስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ መካተታቸውን ያረጋግጣል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ ይገመግማል አቅጣጫ ይሰጣል፤

4) የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት ሥራዎችን ለመፈፀም የሚያስፈልግ በጀት ለባለስልጣኑ በማቅረብ ያፀድቃል፤

5) የማህበራዊ አገልግሎት ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ ተግባራትን አፈጻጸም በየወሩ እና በየሩብ ዓመት በመገምገም ውጤቱ በወቅታዊ ሪፖርት ተካቶ ለባለስልጣኑ እንዲቀርብ ያደርጋል፤

6) ባለስልጣኑ ያወጣውን የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ በተሟላ ሁኔታ ሥራ ላይ ስለመዋሉ ይቆጣጠራል፤ በአግባቡ ስራ ላይ ባይውል ቦርዱ ተጠያቂ ይሆናል።

## 6. የልማት ድርጅቱ ሥራ አመራር ተግባርና ኃላፊነት

የማንኛውም የልማት ደርጅት ስራ አመራር የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፦

1) የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ አፈጻጸሙን ለቦርድ ሪፖርት ያደርጋል፤

2) የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት ሥራዎች በስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ እንዲካተትና ተገቢው የሰው፣ የማቴሪያልና የፋይናንስ ሃብት ለቦርድ አቅርቦ ያፀድቃል፤

3) እንደ ልማት ድርጅቱ ስፋትና ባህሪ የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ በበላይነት የሚያስተባብር የስራ ክፍል እንደ አስፈላጊነቱ ያቋቁማል፤

4) የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት ስራዎች በስትራቴጂክ ዕቅድ እና በድርጊት መርሀ-ግብሮች መሰረት ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑን በመከታተል ለቦርድ ሪፖርት ያቀርባል፤

5) ለአመራርና ሠራተኛው በኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፤

6) የማህበረሰቡንና የባለድርሻ አካላትን ኃላፊነትና የሚኖራቸውን ሚና በተመለከተ የጋራ ዓላማ እንዲያዝና መግባባት እንዲፈጠር ያደርጋል፤ በዕቅድ ዝግጅትና ግምገማም ያሳትፋል፤

7) የልማት ድርጅቱን ሠራተኞች ደህንነት በማስጠበቅና የአካባቢ ማህበረሰብን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት እንዳግባቡ በመቅረጽ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤ ሪፖርትም ያቀርባል፡፡

## 7. የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያስተባብር የስራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት

1) መመሪያው ተግባራዊ እንዲሆን ፈፃሚ አካላትን ያስተባብራል፤ የሚወጡ ፕሮግራሞችን ከሥራ አመራሩ በሚሰጠው አቅጣጫ በበላይነት ይመራል፤

2) ከሚመለከታቸው አካላት የሚቀርቡ የድጋፍ ጥያቄዎች በመመሪያው መሰረት ምላሽ እንዲያገኙ ይከታተላል፤

3) የልማት ድርጅቱን ዓመታዊ የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ ዕቅድና ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ ለበላይ አመራር አቅርቦ ያፀድቃል፤

4) የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት ጥያቄዎችን በመመሪያው በተቀመጠው መስፈርት መሠረት ይገመግማል፤ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤

5) የሥራ ክፍሉ ተቀባይነት ላላቸውም ሆነ ተቀባይነት ለሌላቸው የማህበራዊ አገልግሎት የድጋፍ ጥያቄዎች የግምገማ ሪፖርት ለዋና ስራ አስፈጻሚ ያቀርባል፤

6) እነዚህን ተግባራት የሚያስተባብር የሥራ ክፍል እንደአስፈላጊነቱ በተቋሙ ሊደራጅ ወይም ለሌላ የሥራ ክፍል በተጨማሪ ተግባርነት በሥራ አስፈጻሚው ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አተገባበር ሂደት

### 8. የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት የትኩረት መስኮች፤

በከተማ አስተዳደሩ ህጎች የተደነገጉ ግዴታዎችና ኃላፊነቶች እንደ ተጠበቁ ሆነው የልማት ድርጅቱ ከዚህ በታች በተገለጹ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥተው መስራት ይኖርባቸዋል፡-

1) የማህበራዊ ድጋፎች

2) የኢኮኖሚያዊ ድጋፎች እና

3) የአካባቢ ድጋፎች ፡፡

### 9. የኮርፖሬት ማህበራዊ አገልግሎት መርሆዎች

1) ከአሉታዊ ተጽዕኖ ነጻ፤

2) ዘላቂ ህልውና፤

3) የመልካም ገጽታ ግንባታ፤

4) ከሀብት ብክነት የጸዳ፡፡

### 10. የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት የፋይናንስ ምንጭ

1) የልማት ድርጅቱ ያለፈው በጀት ዓመት ትርፋማ አፈጻጸም ሲኖረው በዓመታዊ ዕቅድ ላይ ለኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት የሚውል በጀት መያዝ አለበት፤

2) በአፈጻጸሙ ትርፋማ ያልሆነ የልማት ድርጅት ለኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት ማከናወኛ በጀት የማይጠይቁ እና በድርጅቱ አቅም ሊፈጸሙ በሚችሉ ድጋፎች ላይ መሳተፍ ይኖርበታል፤

3) ከተለያዩ ተቋማት የሚደረጉ አስገዳጅ ውለታ የተገባባቸው የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት ተግባራትን የልማት ድርጅቱ ሊፈጽም ይገባል፡፡

## 11.የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት ዕቅድ

የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት ዕቅድን ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ዕቅዱ በሚከተለው መሠረት መዘጋጀት ይኖርበታል፡-

1) በጥናት የተለዩ እና ቅድሚያ ትኩረት የተሠጣቸው የኮርፖሬት ማህበራዊ አገልግሎት ጉዳዮች ዝርዝር መለየት፤
2) በጥናት የተለዩ እና ቅድሚያ ትኩረት የተሠጣቸው የኮርፖሬት ማህበራዊ አገልግሎት ጉዳዮች ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመወያየት ሊለኩ የሚችሉ ዓላማዎችን በማስቀመጥ በዕቅድ ማካተት፤
3) የተቋሙንና የባለድርሻ አካላትን ሚና በግልጽ ለይቶ የሥራና የሃላፊነት ድርሻ በግልጽ ማስቀመጥ፤
4) በዕቅድ የተያዙ ድጋፎችን ለመተግበር የሚያስፈልጉ ወጪዎችን መወሰንና በጀት አፀድቆ መመደብ፤
5) የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ ዕቅድና መርሀ ግብር ማዘጋጀት፤
6) የዕቅዱን የድጋፍና ክትትል ስርዓት መዘርጋት፡፡

# ክፍል አራት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 12.በኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አገልግሎት አሰጣጥ የተከለከሉ ተግባራት

ማንኛውም የልማት ድርጅት ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ጉዳዮች ምንም ዓይነት ድጋፍ አይሰጥም፡-

1) ለኃይማኖት ተቋማት የሚደረግ ድጋፍ፤
2) የዘር፣ የቀለም፣ የቋንቋ ወይም በማንኛዉም ምክንያት ልዩነት ሊያሰፉ ለሚችሉ ተግባራት የሚሰጥ ድጋፍ፤

3) ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚደረግ ድጋፍ፤

4) የህዝብ ደህንነትና ጸጥታ አደጋ ውስጥ ለሚከቱ እንቅስቃሴዎች የሚሰጥ ድጋፍ፤

5) የህዝብን ሞራል እና እምነት ለሚጻረር ድርጊት የሚሰጥ ድጋፍ፤

6) ድርጅቱን ለታወቀ ወይም ላልታወቀ ዕዳ የሚዳርግ ድጋፍ፡፡

13. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎችና አሰራሮች</u>

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ባለሥልጣኑ ያወጣው መመሪያና ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

14. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

ባለስልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

15. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለስልጣን ድህረ ገጽ ላይ ከተጫነበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ……ቀን 2017ዓ.ም**

**አቶ ተንኩዌይ ጆክ ሮም**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**

**የመንግስት የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለስልጣን**

**ዋና ሥራ አስፈጻሚ**